አባሪ : ወደ ማቀናጀት ዕቅድ መመሪያ

# በመግቢያ ፕሮግራም ውስጥ ለሚሳተፉ ስለ ውህደት እቅድ መረጃ

## ስለ ውህደት እቅድዎ

- እርስዎ እና አውራጃው በጋራ መሥራት የውህደት እቅድ የሚሆንዎትን በመስተዋወቂያው እቅድ ውስጥ ተካፋይነትዎትን በሚመለከት እቅድን ታዘጋጃላችሁ ፡፡ በመተዋወቂያ እቅዱ ውስጥ መሳተፍዎ ጥሩ የኖርዌይ ቋንቋ ችሎታዎችን ፣ ስለ የኖርዌይ ህብረተሰብ ዕውቀትን ፣ መደበኛ የትምሕርት ብቃቶችን እና ከሥራ ሕይወት ጋር ዘላቂ ግንኙነት እንዲኖርዎ አስተዋፅዖ ያደርግልዎታል ፡፡ ዋናው ግቡ ግን እርስዎ በአክችጭር ጊዜ ውስጥ ከኖርዌይ ህብረተሰብ ጋር ተቀናጅተው በምጣኔ ሐብት ወይም በገንዘብ እራስዎትን የቻሉ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

## የብቃት ግምገማ

- የእርሷዎ የውህደት እቅድ ከመዘጋጀቱ በፊት የብቃት ግምገማ እንዲደረግ  የማድረግ መብት እና እንዲሁም ግዴታ አለብዎት ፡፡ይሕም የግምገማ ጥናት ቢያንስ ቢያንስ የቋንቋ ችሎታ እና ምን ዓይነት ትምህርት ፣ የሥራ ልምድ እና ሌሎች ተገቢ ወይም አስፈላጊ ችሎታ እንዳሎት ማካተት አለበት ፡፡

## የሥራ መመሪያ

- የሙያ መመሪያን የሚሰጥበት ላይ የመካፈል መብት እና እንዲሁም ግዴታ አለብዎት ፡፡ የሙያ መመሪያው ለስራ እና ለትምህርት እቅድ ማውጣት እንዲችሉ መረጃ የማግኘት እድልን እንዲያገኙ ይረድዎታል።

## የውህደት እቅድዎ ይዘት

- የውህደት እቅዱ የመጨረሻ ግብዎን እና የኖርዌይ ቋንቋን ግብዎን ፣ የሥልጠና የትምሕርት ዕቅድ ፣ በእቅዱ ላይ ለምን ያህል ጊዜ መሳተፍ እንደሚችሉ እና የይግባኝ አማራጮችዎን ማካተት አለበት ።እቅድዎ በትምህርትዎ ፣በስራዎ ልምድ ፣ ከሥራ ሕይወት ጋር በተያያዙ ክህሎቶች እና በሌሎች ተዛማጅ  መረጃዎች ቅኝት ወይም ግምገማ  ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ፡፡

  የማስተዋወቂያ እቅዱ ቢያንስ ቢያን የሚመለከቱትን ማካተት አለበት
  ሀ) የኖርዊጂያን ቋንቋ ሥልጠና
  ለ) ስለ የኖርዊጂያን ማሕበረሰብ ጥናት ሥልጠና
  ሐ) የሕይወት ወጣ ወረዶችን ለመቋቋም የሚያበቃ ስልጣኔ
  መ) ሥራ-ወይም ትምህርት-ተኮር አካላት።
  ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ያላቸው ተሳታፊዎች ለወላጆች ልጅ የመሳደግ የመመሪያ ስልጠና  ውስጥ መሳተፍ ይጠበቅባቻዋል፡፡

የማስተዋወቂያ እቅድ መርሃ ግብር ዓመቱን በሙሉ የሚካሔድ ሲሆን እንደዚሁም እንደ ማንኛውም ስራ በሙሉ ጊዜ መሆን አለበት።

## የእርስዎ የመጨረሻ ግቢ

- አውራጃው በማስተዋወቂያው እቅድ ውስጥ በሚካፈሉበት ወቅት የመጨረሻ ግብዎን ማውጣት ይኖርበታል ፡፡ ይኽ የመጨረሻው ግብ የሚወሰነው ከዚህ ቀደም ሲል በነበረዎት ትምህርት ደረጃ መሠረት ላይ በመመስረት ነው ፡፡

### የኖርጂያን ቋንቋ ስለጠና ግብ

- በኖርዊጂያን ቋንቋ ሥልጠና ተሳታፊዎች በኖርዊጅያን ቋንቋ ዝቅተኛ ደረጃውን ቢያንስ ቢያንስ መድረስ አለባቸው ፡፡ የአውራጃው ገገርና እና አውራጃው ወይም ኳሚውኑ ይኸንን ዝቅተኛውን ደረጃ ተብሎ የታቀደውን የቋንቋ እውቀት ተሳታፊውች በማግኘት ብቃት እንዲያገኝ አስፈላጊውን ያደርጋሉ ወይም ያቀርባሉ ፡፡

### የውህደት እቅድዎ ተካፋይነት ተገቢው ክትትል ወይም ድጋፍ ስለ ማግኘትና እና ግምገማ

- በስልጠናው ወቅት አውራጃው ስለ ውህደት እቅድዎ በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንዳለና የሚጠበቀበትን በቂ አገልግሎት እያገኙበት እንደሆነ ለማጣአራት ከእርስዎ ጋር ውይይቶችን ያካሂዳል ፡፡ የውህደት እቅድዎ ላይ ካልተከተሉ ወይም እቅድዎን ለመቀየር አሳብ ወይም ፍላጓት ከአሎት ወዲያውኑ በተቻለ ፍጥነት ከርሷ ተጠሪ ጋር መገናኘትና መነጋገር አለብዎት።

### ስለ ውህደት እቅድዎ አቤቱታ ወይም ቅሬታን ማቅአረብን ይፈልጋሉ ?

- ስለ የቀረበልዎ ሥልጠናውም ሆነ ስለ ውህደት ዕቅድዎ ይዘት አቤቱታ ወይም ቅሬታ ከአልዎት ማቅረብ ይችላሉ ፡፡

### ቅሬታ ወይም አቤቱታ ከአልዎት የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት:

- ስለ ውህደት እቅድዎ ይዘት ውሳኔ ከደረስዎበት ቀን አስቶ በሶስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ቅሬታዎን ወይም አቤቱታዋን ያቅርቡ
- የውኸደት እቅድዎ ላይ ውሳኔ ለወሰደው ወይም ለሰጥው በአወራጃው ለሚገኘው የመንግስት አካል ቅሬታውን ያቅርቡ
- ቅሪታዋ ምን ላይ እንደሆነ በግልጽ ይግለጡ
- ቅሬታውን በጹሁበመፍ ከማቅረብዎ በፊት መፈረም አለብዎት

ጠበቃም ከአሎት እርስዎን ወክሎ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል ፡፡ አንድ ሰው እንደ ተወካይዎ ሆኖ ለእርስዎ አቤቱታ እንዲጽፍሎት ለዚያ ግለሰብ በጽሑፍ ተወካይ ለመሆኑ ፈቃድ መስጠት አለብዎት ፡፡ይኸ የውክልና ስልጣን ላይ ውክልና የተሰጠው ግለሰብ እርስዎን ወክሎ ምን ምን ማድረግ እንደሚችል መግለጽ አለበት ፡፡ ጠበቃ ካለዎት የውክልና ስልጣን አያስፈልግም።

### ስለ ውህደት እቅድ ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት ይችላሉ?

ስለ ውህደት እቅድ ተጨማሪ መረጃ ስለ ውህደት በወጣው ህግ ውስጥ ይገኛል ፡፡ ህጉ አብሮ ሆኖ ከወጣው የጹሁፍ ስርጭቶች ጋር በ www.imdi.no እና በኖርዌ በብቃት ድረ ገጽ ወይም (Kompetanse Norge nettsider) ያገኛሉ።

በስልጣናው ላይ መልካም ዕድል እንመኛለን!